በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት

የ 2015 የክረምት ንቅናቀ ትምህርት ለትውልድ ሪፖርት

ሀምለ 18/2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ክፍልአንድ

1. መግቢያ

ትምህርት ለትውልድ የመጀመሪያ ሪፖርት ወረዳ 11

በትምህርት ዘርፍ ላይ የተሰሩ ጥናቶችና እንዲሁም የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ የትምህርት ጥራት በርካታ ችግሮች እንዳሉበትና አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱን አመላክተዋል።የተለዩት የትምህርት ጥራት ችግሮች ውስጥ የሥርዓተ-ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ ከምርትና ከተግባር ጋር የተያያዘ አለመሆን፣ የመምህራን ብቃትና ተነሳሽነት ችግር፣ ትምህርት ቤቶች በሚፈለገው መጠን ለመማር ማስተማር ምቹ አለመሆናቸው በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

የጥራት መጓደል ምክንያት የሆነው ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር በሚፈለገው ልክ ምቹ አለመሆን የብዙ አካላትን ተሣትፎ የሚጠይቅ ነው። ይህንን ችግር ለማሻሻል እና ዘላቂ መፍትሔ ለማበጀት የማህበረሰብና የልዩ ልዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ቀጥተኛ ተሣትፎን ያማከለ ንቅናቄ ማድረግ እጅግ ወሳኝ ሆኖ ተገኝቷል። ስለሆነም የ 2015 ዓ.ም ትምህርት ለትውልድ የክረምት ንቅናቄ እስከ አህን የተከናወኑ ተግባራትን በዚህ መስረት እደሚከተለው ሪፖርቱን ለማዘጋጀት ተችሏል።

2. የሪፖርቱ አላማ

1. በየደረጃው ባለው ማህበረሰብና ልዩ ልዩ አካላት ተሳትፎ የትምህርት ቤቶችን መሠረተ-ልማት (ንፁህ የመጠጥ ውሃ፣ መፀዳጃ ቤቶች፣ በቂ መማሪያ ክፍሎች፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፤ የስፖርት ሜዳ፣ ማጣቀሻ መጻሕፍት፣ የኤሌትሪክ አገልግሎት፣ ቤተ-መጻሕፍት፣ ቤተ-ሙከራ፤ አጥር፤ምድረ ግቢ ማስተካከልና ማስዋብ፤አዋኪ ድረጊቶችን ማጽዳት፤ ወዘተ.)
2. የአሠራር ሥርአት ተዘርግቶ ሥራው በዘላቂነት እንዲቀጥልና ማህበረሰቡ በትምህርት ሥርአት ውስጥ በመሠረተ-ልማት መሻሻል ሳይወሰን የመማር ማስተማሩን ሂደት በባለቤትነት እንዲደግፍ ለማስቻል ነው።

3. የሪፖርቱ አስፈላጊነት

የ 2015 በጀት ዓመት የትምህርት ስራ ትምህርት ለትውልድ በሚል መሪ ቃል የክረምት ንቅናቄ የደረሱበትን ደረጃ በመለየት እና ያልተከናወኑትን ደግሞ ለሚቀትሎ ወራት ውስጥ እንዴት ማከናወን እንዳለባቸው በየደረጃው የመፈፀም እና የማስፈፀም ስርዓት ለመዘርጋት ትምህርት ለትውልድ ስራዎች ያሉበትን ደረጃ ሪፖርት ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቶዋል።

4. የሪፖርት ወሰን

ይህ ሪፖርት በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ወረዳ 11 ትምህርት ጽ/ቤት ቆጣሪ ቅድመ መጀመሪያ ደረጃ እን ቆጣሪ የመጀመሪያ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተከናወኑ ተግባራትን ተፈፃም ይሆናል።

5. የሴክተሩ ተልዕኮ፣ራዕይ እና ዕሴቶች

5.1 ተልዕኮ፡-

የትምህርት ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ፤ የትምህርት ተቋማትን በፍትሃዊነት በማዳረስና ተገቢ ድጋፍና ክትትል በማድረግ፤ በቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ አለማቀፍ ደረጃውን የጠበቀ፣ ብቃትና ጥራቱ የተረጋገጠ አጠቃላይ ትምህርት በተሰማሚ ፕሮግራሞች ለክፍለ ከተማው ነዋሪ መስጠት።

5.2 ራዕይ፡-

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ውጤታማ የትምህርት ሥርዓት በማስፈን በ2022 ዓ.ም ዓለም ዓቀፋዊ ተወዳዳሪ የሆኑ የትምህርት ተቋማትና በልማትበዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር ግንባታ ቁልፍ ሚና የሚጫወቱ የተሟላ ስብዕና ያላቸው ዜጎች ማፍራት።

5.3 እሴቶች፡-

- ለለውጥ ዝግጁነን፣
- ለትምህርት ጥራት ቅድሚያ እንሰጣለን፣
- ጥናትና ምርምር የችግሮቻችን መፍቻነው፣
- በእውቀትና በእምነት እንመራለን /እንሠራለን፣
- በግልጽነት እና ገለግላለን፣
- የተጠያቂነት ስርዓትን እናሰፍናለን፣
- ለላቀ አገልግሎት እንተጋለን፣ እንሰጣለን
- በጋራ መስራት መገለጫችን ነው፣
- መልካም ሥነ-ምግባር የዜጎቻችን መለያ ነው፣

ክፍል ሁለት

6.ትምህርት ለትውልድ እስከ አሀን የተከናወኑ ተግባራት በተመለከተ

6.1 የንቅናቀ እቅድ በተመለከተ

- የእቅድ ዝግጅት በማድረግ የወረደውን እቅድ ወደ እራሳችን በመቀየር እቅድ መዘጋጀት ተችሏል።
- ትምህርት ቤቱ እቅድ እንዲያዘጋች ተደረጎዋል።
- እቅዱን ከሚመለከተው ባለድርሻ አካልት ጋር የጋራ ማድረግ ተችሏል።

ለምሳሌ ፡- ከወላጅ ተማሪዎች ፤ከወ.ተ.ማ፤ ከወረዳ አመራር ፤ ሱ/ቫዘሮች የትምህርት አመራርና ባለሙያዎች እና ከወረዳ ባለሀብቶች ጋር የጋራ ተደርጎዋል።

6.2 አደራጃጀት በተመለከተው

- ❖ የወረዳ አመራሮች የዚህ እቅድ አባል ኮሚቴ ናቸው።
- ❖ የትምህርት አመራሮች እና ሱ/ቫዜሮች በሙሉ የዚህ ኮሚተ አባል ናቸው።
- ❖ የትምህርት ቤቱ ወ.ተ.ማ የዚህ ኮሚተ አባል ናቸው።
- ❖ ሌላው ደግም እንደ አስፈላጊነቱ ተፅኖ ፈጣሪ ከሁሉም አምስት አባል ያለውን መቋቀም ተችሏል።

6.3 እስከ አሀን የተከናወኑ ተግባራት በተመለከተ

- ✓ የትም/ቤቱ የስፖርት ሜዳ ማስተካከል
- ✓ አንድ የመምህራን መዝናኛ ማስተካከል ተችሏል።
- ✓ እስከ አሁን ከተማሪዎች ወላጅ ወደ 500000 ብር መሰብሰብ መቻሉ እና ስራ መገባቱ።
- ✓ 16 የሽንት ቤት ቀዳዳዎች አፈርሶ የማስራት ስራ ተሰርቶዋል

ክፍል ሶስት

7.እስከ አሁን የታዩ ጠንካራጎኖች እና ውስንነቶች በተመለከተው

በጥንካሬ የታዩ

- ✓ የሳምንት ስራዎችን በመገምገም የትኩረት አቅጣጫ ማስቀመጥ መቻሉ።
- ✓ ስራዎችን ቆጥሮ በመስጥ ቆጥሮ ለመቀበል ጥረት መደረግ መቻሉ ።
- ✓ ቋሚ የግንኙነት ጊዜ በማስቀመጥ ተቀራራቢ ውጤትና የውድድር መንፈስ እንዲመጣ ማስቻሉ።
- ✓ የክ/ከተማ አመራር ቋሚነት ድጋፍ እያደረግልን መሆኑ።
- ✓ የስፖርት ሜዳ መጀመሩ እና እስከ አሁን ከተማሪዎች ወላጅ ወደ 500000 ብር መሰብሰብ መቻሉ እና ስራ መገባቱ።

በውስንነት የታዩ

- ✓ እስካ አሁን የተሰሩ ስረሰዎች ከእቅዱ አንፃር ውስንነት መኖሩ።
- ✓ በየደረጃ ያሉ አደራጃጀቶች ትኩረት ያለመስጣት ውስንነት መኖሩ።

ያጋጠሙች ግሮች

- የትምህርት ለትውል ሌሎች ይደግፉሉ የተባሉ በየደረጃ ያሉ የባለድርሻ አካላት ትኩረት ያለመስጣትና ለትምህርት ተቋም ብቻ የመተው ችግሮች ይታያሉ።

የተወሰደ መፍትሔ

- በየደረጃ ያሉ የባለድርሻ አካላት ትኩረት እንዲሰጡ በየጊዜ እንዲ ገመገም በማድረግ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ ።

የቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ

- ካጋጠሙ ችግሮች ፈጥነን በመውጣት ወደ ስራ መግባት ያስፈልጋል።
- የክ/ከተማ አስተባባር ኮሚቴ እና የወረዳ አስተባባር ኮሚቴ ፈጥኖ ወደ ስራ እንዲገቡ እና ለትምህርት ስራ ትኩረት ሰጦ ሌሎች ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ።

ማጠቃለያ

የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ትምህርት ጽ/ቤት በ 2015 የትምህርት በጀት አመት ትምህርት ለትውልድ በሚል መሪ ቃል የትምህርት ቦቶች መሠረተ ልማት ማሻሻል በመንግስት የቀረጸውን አዲስ ስትራቴጅ ለሁሉም ዜጎች በፍትሃዊነት ለማዳረስና ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርግ መቆየቱ ይታወቃል። በመሆኑም በመማር ማስተማሩ ዙሪያ የትምህርት ቤቶችን የመማር ማስተማር ስራው በተሳለጠ ሁኔታ ለማስቀጠል ባሉን አቅም በመጠቀም የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ የተሻለ ስራ ለመስራት ጥረት ተደርጓል።

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት የ 2015 የክረምት ንቅናቄ ትምህርት ለትውልድ ሪፖርት

ተ.ቁ	የትምህርት ቤቱየተለዩ የችግሮች	ድጋፍ ያደረጉ አካላት ስም	ድጋፍ የፈጀው ብር	ተግባሩ ያለበት አፈፃፀም	ክ/ከተማ ያለበት አፈፃፀም			ያጋጠሙ ችግሮች
					አረንጓዴ	ቢጫ	ቀይ	
1.	በቀን 300 ሺ ሊትር የንፁህ ውሃ አቅርቦት							
2.	የአይ.ሲ.ቲ ግባቶች ተጨማሪ ያስፈልጋል (60 ኮምፒውተር)							
3.	የትም/ቤቱ የስፖርት ሜዳ	ወ/ተማሪ	500,000	60%	✓			
4.	የኤሌክትሪክ አገልግሎት ተጨማሪ ያስፈልጋል							
5.	የሴት ተማሪዎች ንፅህና መጠበቂያ የግብአት ችግር							
6.	500 የተማሪዎች መቀመጫ ወንበር ተጨማሪ ያስፈልጋል							
7.	3 የማባዥ ማሽን ተጨማሪ ያስፈልጋል							
8.	20 የሳይንስ ኪት ተጨማሪ ያስፈልጋል							
9.	30 ሬዲዬኖች ተጨማሪ ያስፈልጋል							
10.	1000 በአዲሱ ሥርዓተ ት/ት አጋዥ/ማጣቀሻ መፅሀፍት ተጨማሪ ያስፈልጋል							
11.	200 የት/ት ማበልፀጊያ ማዕከል ግብአት ተጨማሪ ያስፈልጋል							
12.	55 የልዩ ፍላጎት ግብአት ተጨማሪ ያስፈልጋል							
13.	የት/ቤቱ የማመሪያ ክፍል በር እና ወንበሮች እድሳት							
	ለ. በመካከለኛ ጊዜ የሚፈቱ ችግሮች							
14.	1 የልዩ ፍላጎት መስጫ ማዕከል ግንባታ ያስፈልጋል							
15.	የትም/ቤቱ አጥር ተጨማሪ እድሳት ያስፈልጋል							
16.	6 ራምፕ ተጨማሪ ያስፈልጋል							
17.	50 የተለያዩ የመ/ራን እና የቢሮ ጠረጴዛ ተጨማሪ ያስፈልጋል							
18.	60 ለመ/ራን ወንበር ተጨማሪ ያስፈልጋል							
19.	10 ፕሪንተር ተጨማሪ ያስፈልጋል							
20.	2 ቴሌቭዥን ተጨማሪ ያስፈልጋል							
21.	20 GB ኢንተርኔት ያስፈልጋል							
22.	35 የላቦራቶሪ ኬሚካል ተጨማሪ ያስፈልጋል							
23.	25 የላቦራቶሪ መሳሪያ ተጨማሪ ያስፈልጋል							
	ሐ. በረጅም ጊዜ የሚፈቱ ችግሮች							
24.	24 የተማሪዎች የመማሪያ ክፍል ተጨማሪ ግንባታ ያስፈልጋል							
25.	1 ቤተ መጻህፍት በተጨማሪ ግንባታ ያስፈልጋል							
26.	1 ለአንደኛ ደረጃ ትም/ቤት ቤተ ሙከራ ግንባታ ያስፈልጋል							
27.	1 የትምህርት ማበልጸጊያ ማዕከል ተጨማሪ ግንባታ ያስፈልጋል							
28.	ባለ 24 የወንድ እና ባለ 24 የሴት ተማሪዎች የመጸዳጃ ቤት ተጨማሪ ግንባታ ያስፈልጋል							
29.	ባለ 12 የወንድ እና ባለ 12 ሴት የኬጂ መምህራን መጸዳጃ ቤት							
30.	1 የር/መ/ር ቢሮ ተጨማሪ ያስፈልጋል							
31.	1 የም/ር/መ/ር/ራን ቢሮ ተጨማሪ ያስፈልጋል							

32.	1 የመምህራን ማረፊያ ክፍል							
33.	2 የአስተዳደር ሰራተኛ ክፍል							
34.	2 የእቃ ግምጃ ቤት ተጨማሪ ግንባታ ያስፈልጋል							
35.	4 የትምህርት ክፍሎች (Deparetements ተጨማሪ ያስፈልጋል							
36.	25 መደርደሪያዎች (ሸልፎች) ተጨማሪ ያስፈልጋል							
37.	10 ካፕቦርድ ተጨማሪ ያስፈልጋል							
38.								